የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፱
አዲስ አበባ ነሐሴ ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22[nd] Year No.79
ADDIS ABABA 9[th] August , 2017

<u>ማውጫ</u>

ደንብ ቁጥር ፬፻፯/፪ሺ፱ ዓ.ም

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌደራል የታክስ አስተዳደር ደንብ......................................................ገጽ ፱ሺ፰፻፴

## Content

Regulation No.407/2017

Council of Ministers Federal Tax Administration Regulation ......................................................Page 9830

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፯/፪ሺ፱**

## <u>ስለ ፌደራል የታክስ አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፫/፪ሺ፰ አንቀጽ ፻፴፮ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ</u>

**፩.<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌደራል የታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፬፻፯/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪.<u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "አዋጅ" ማለት የፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፫/፪ሺ፰ ነው፤

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO.407/2017**

## <u>COUNCILS OF MINISTERS TAX ADMINISTRATION REGULATION</u>

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.916/2015 and Article 136 of the Federal Tax Administration Proclamation No. 983/2016.

### <u>PART ONE</u>

### <u>GENERAL</u>

**1. <u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as "the Council of Ministers Federal Tax Administration Regulation No.407/2017".

**2. <u>Definition</u>**

Unless the context requires otherwise, in this Regulation:

1) "Proclamation" means the Federal Tax Administration Proclamation No.983/2016;

፪/ "የተሻረው አዋጅ" ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ እንደተሻሻለ)፣ የማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር ፶፫/፲፱፻፹፭ ከነ ማሻሻያዎቹ እና የነዳጅ ሥራዎች አዋጅ ቁጥር ፺፮/፲፱፻፸፰ ከነማሻሻያዎቹ ናቸው።

፫/ በዚህ ደንብ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሀረጎች እንደአግባብነታቸው በአዋጁ ወይም በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፱/፪ሺ፰ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

## ክፍል ሁለት

## የታክስ ሕጎችን ስለማስተዳደር

### ፫.ሚስጥራዊ መረጃ ስለመስጠት

የአዋጁ አንቀጽ ፰(፪) እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ሚስጥራዊ ሰነድ ወይም መረጃ ሊሰጥ የሚችለው ጥያቄው በጽሑፍ ለዋና ዳይሬክተሩ ወይም እሱን ለሚወክለው ሰው ሲቀርብ እና ሲፈቀድ ብቻ ነው።

## ክፍል ሦስት

## ምዝገባ

### ፬.የማንነት የሰነድ ማስረጃ

፩/ማንኛውም ግለሰብ ከሚያቀርበው የምዝገባ ማመልከቻ ጋር ከሚከተሉት አንዱን የማንነት የሰነድ ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ አለበት፦

ሀ) ወቅታዊ የግለሰቡ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም የግለሰቡን የግል መረጃ የያዘ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ አገር ፓስፖርት ገፅ የተረጋገጠ ቅጂ፤ ወይም

ለ) የግለሰቡ ወቅታዊ የኢትዮጵያ የመንጃ ፈቃድ የተረጋገጠ ቅጂ፤ወይም

ሐ)የግለሰቡን የግል መረጃ የያዘ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት ወቅታዊ የሌላ ሀገር የመንጃ ፈቃድ ገጽ የተረጋገጠ ቅጂ፤ ወይም

2) "Repealed Proclamation" means the Income Tax Proclamation No.286/2002 (as amended), Mining Income Tax Proclamation No.53/1993 and all amendments there to and Petroleum Operations Income Tax Proclamation No.96/1986 and all amendments thereto.

3) A term used in this Regulation shall have the same meaning as in the Proclamation or the Federal Income Tax Proclamation No.979/2016, as the case may be.

## PART TWO

## ADMINISTRATION OF TAX LAWS

### 3. Supply of Confidential Information

Without prejudice to Article 8(2) of the proclamation, the Authority shall provide a confidential document or information only when a written request is submitted to the Director General or his representative and the provision of the document or information is authorized.

## PART THREE

## REGISTRATION

### 4. Documentary Evidence of Identity

1/ An application for registration by an individual shall be accompanied by any of the following documentary evidence of identity:

a) the individual's current residence identity cardor certified copy of the page of the Ethiopian or foreign current passport containing the individual's personal information; or

b) certified copy of the individual's current Ethiopian driver's licence ; or

c) certified copy of the page of the individuals current foreign driver's licence containing personal information of the individual and to which the photograph of the individual is attached; or

መ) የግለሰቡ የተረጋገጠ የልደት የምስክር ወረቀት ቅጂ፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም ባለስልጣኑ አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ሌላ ማንኛውም ማስረጃ እንዲያቀርብለት አመልካቹን ሊጠይቅ ይችላል።

፫/ በኩባንያ የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ኩባንያው የተቋቋመበትን ወይም የተመዘገበበትን የምስክር ወረቀት ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ ማቅረብ አለበት።

፬/ በሽርክና ማህበር የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ከሽርክና ማህበሩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

፭/ በሌላ ማንኛውም ድርጅት የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ ከድርጅቱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ማንኛውም የመመስረቻ ወይም ማቋቋሚያ ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

**፭. የማንነት አካላዊ መረጃ**

፩/ ለግለሰብ ምዝገባ ዓላማ ባለሥልጣኑ፦

ሀ) የግለሰቡን ትክክለኛ ማንነት ለማረጋገጥ፤ ወይም

ለ) የማንነት ስርቆትን ወይም ማጭበርበርን ለመከላከል፤ አመልካቹን ግለሰብ የማንነት አካላዊ መረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል።

፪/ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ከግለሰብ ጋር በተገናኘ "የማንነት አካላዊ መረጃ" ማለት የግለሰቡን ማንነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውል የግለሰብ ማንነት መለያ አካላዊ መረጃ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፦

ሀ) የፊት ገጽታ መለያ፤

ለ) የጣት አሻራ መለያ፤

ሐ) የድምፅ መለያ፤

d) certified copy of the individual's birth certificate;

2/ Notwithstanding the provision of sub article (1) of this article, the Authority may require the applicant to submit such other evidence as it deems necessary.

3/ An application for registration by an incorporated company must be accompanied by the certificate of incorporation or registration of the company.

4/ An application for registration by a partnership must be accompanied by the partnership deed.

5/ An application for registration by any other body must be accompanied by the certificate of registration, or other document of formation or creation.

**5. Biometric Information**

1/ For the purposes of registration of an individual, Authority may require an individual to submit biomet information so as to:

a) ensure the proper identification of individual; or

b) counteract identity theft or fraud.

2/ In this Article, "biometric information", in relation to individual, means biological data to authenticate identity of the individual, and may include following:

a) facial recognition;

b) fingerprint recognition;

c) vocal recognition;

መ) የዓይን ክፍሎች (ምጣኔ ብርሃን ወይም መቅረፀ ምስል) መለያ።

## ክፍል-አራት
## የታክስ እንደራሴዎች

**፮.ነዋሪ ያልሆነ ሰው የታክስ እንደራሴ**

፩/ ለአዋጁ አፈፃፀም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ ፬(፬) መሠረት በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት 'ወኪል' ተብሎ በሚጠራ ሰው አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚያከናውነው የንግድ ሥራ ወኪሉ ነዋሪ ያልሆነው ሰው የታክስ እንደራሴ ተደርጎ ይቆጠራል።

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት እንደታክስ እንደራሴ የሚቆጠር ነዋሪ ያልሆነ ሰው ወኪል በገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ ፪(፵) መሠረት ነዋሪ ያልሆነ ሰው የታክስ እንደራሴ ከሆነ ሌላ ማንኛውም ሰው ተጨማሪ እንደተሰየመ የታክስ እንደራሴ ሆኖ ይቆጠራል።

## ክፍል አምስት
## የከባድ ችግር ሁኔታዎች

**፯. የታክስ ምህረት ገደብ**

ሚኒስትሩ በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ መሠረት የሚሰጠው የታክስ እና የዘገየ ክፍያ ወለድ ምህረት የገንዘብ ጣሪያ ፲ ሚሊዮን (አስር ሚሊዮን) ብር ይሆናል።

## ክፍል ስድስት
## ማስታወቂያዎች እና የታክስ ክፍያ

**፰. የሰነዶች አቀራረብ እና የታክስ አከፋፈል ሥርዓት**

በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም ሰው ታክስ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ በሚከተለው አኳኋን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ እና ታክስ መክፈል አለበት፦

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፹፪(፪) ተፈፃሚ በሚሆንበት ሁኔታ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በማስተላለፍ ወይም የአዋጁን

d) iris or retina recognition.

## PART FOUR
## TAX REPRESENTATIVES

**6. Tax Representative of a Non-Resident**

1/ For a non-resident conducting business in Ethiopia through the activities of a person (referred to as the "agent") constituting a permanent establishment in Ethiopia of the non-resident under Article 4(4) of the Federal Income Tax Proclamation, the agent shall be tax representative of the non-resident for the purposes of the Proclamation.

2/ The treatment of an agent as the tax representative of non-resident under sub-article (1) of this Article shall be in addition to any other person treated as the tax representative of the non-resident under Article 2(40) of the Proclamation.

## PART FIVE
## HARDSHIP CASES

**7. Limit to Remission of Tax Debt**

The maximum amount of tax debt and late payment interest that the Minister may remit under Article 51 of the Proclamation shall be 10,000,000 (Ten Million) birr.

## PART SIX
## NOTICES AND PAYMENT OF TAX

**8. Manner of Filing Documents and Paying Tax**

Except as otherwise provided in the Proclamation or this Regulation, a person shall file a tax declaration or other document with the Authority and pay tax in the following manner:

1/ when Article 82(2) of the Proclamation applies, by electronic transmission or payment in accordance with the directions of the Authority under that Article; or

አንቀጽ መሠረት አድርጎ ባለሥልጣኑ የሚሰጠውን መመሪያ በመከተል ክፍያ መፈጸም፤ ወይም

፪/ በሌላ ማንኛውም ሁኔታ በአካል በማቅረብ ወይም በፖስታ ለባለሥልጣኑ በመላክ፡፡

## ክፍል ሰባት

## የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን

## ምዕራፍ አንድ

## ኮሚሽኑ በይግባኝ ሰሚ ሂደት ያለው ሥልጣን

**፱.የኮሚሽኑ ሥልጣን**

፩/ ኮሚሽኑ፦

ሀ) ማስረጃ በቃለ መሃላ ወይም በማረጋገጫ መቀበል፤

ለ) የዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩(፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ስለሰሚ ሂደቱ ማስታወቂያ በአግባቡ ደርሶት ያልቀረበ ወገን በሌለበት የሰሚ ሂደቱን መቀጠል፤ ወይም

ሐ) የሰሚ ሂደቱን በቀጠሮ ማስተላለፍ፤

ይችላል፡፡

፪/ የኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት ማንኛውም ሰው በኮሚሽኑ የሰሚ ሂደት ቀርቦ ማስረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

፫/ በኮሚሽኑ የሰሚ ሂደት እንደምስክር ቀርቦ ማስረጃ እንዲሰጥ መጥሪያ የደረሰው ሰው በኮሚሽኑ መመሪያ መሠረት ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለተጠራ ምስክር የሚከፈለው ያህል የውሎ አበል ክፍያ ይፈፀምለታል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የኮሚሽኑ ውሳኔ

**፲. የይግባኝ ማመልከቻ ስለማቋረጥ ፣ ስለመዝጋት ወይም እንደገና ስለማየት**

፩/ ማንኛውም ይግባኝ ባይ ለኮሚሽኑ የቀረበውን ይግባኝ በማናቸውም ጊዜ ለኮሚሽኑ ሬጅስትራር የጽሑፍ ማስታወቂያ በማቅረብ ማቋረጥ ወይም መተው የሚችል ሲሆን፣ ኮሚሽኑም ይህ

2/ in any other case, by personal delivery or post to an office of the Authority.

## PART SEVEN

## TAX APPEAL COMMISSION

## CHAPTER ONE

## POWERS OF THE COMMISSION ON A HEARING

**9. Powers of the Commission**

1/ The Commission may:

a) take evidence on oath or affirmation;

b) subject to Article 11(2) of this Regulation, proceed the absence of a party who has had reasonable notic of a hearing; or

c) adjourn a hearing from time to time.

2/ The President of the Commission may summon a pers to appear before the Commission at a hearing to gi evidence.

3/ A person summoned to appear as a witness before Commission shall be entitled to be paid fees at su rates as are allowable for witnesses in the Federal H Court in accordance with the directive of Commission.

## CHAPTER TWO

## DECISION OF THE COMMISSION

**10. Discontinuance, Dismissal, or Reinstatement of Appea Application**

1/ An appellant may discontinue or withdraw an appea to the Commission at any time by filing written notic with the Registrar of the Commission and th Commission shall dismiss the appeal.

በሚሆንበት ጊዜ ይግባኙን ይዘጋል።

፪/ የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም ሰው በኮሚሽኑ የስሚ ሂደት በአካል ወይም በወኪሉ አማካኝነት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ኮሚሽኑ ይግባኙን መዝጋት ይችላል።

፫/ የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ከይግባኙ ጋር በተገናኘ ኮሚሽኑ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ያልፈጸመ እንደሆነ፣ ፕሬዚዳንቱ ስለኮሚሽኑ ሆኖ ይግባኙን መዝጋት ይችላል።

፬/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም (፫) መሠረት ይግባኝ የዘጋ እንደሆነ፣ ይግባኝ ባዩ የይግባኙ መዘጋት ማስታወቂያ በደረሰው በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ይግባኙ እንደገና እንዲታይለት ለኮሚሽኑ ማመልከት ይችላል።

፭/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ማመልከቻ የቀረበ እንደሆነ፣ በፕሬዚዳንቱ የሚሰጥ ማንኛውም ትዕዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ይግባኙን እንደገና ሊያይ ይችላል።

## ፲፩. በተከራካሪ ወገኖች መካከል ስለሚደረግ ስምምነት

በይግባኙ ስሚ ማንኛውም ደረጃ ከይግባኙ ወይም ከይግባኙ ክፊል ጉዳይ ጋር በተገናኘ ኮሚሽኑ ስለሚሰጠው ውሳኔ ሁኔታዎች ተከራካሪ ወገኖች በጽሑፍ የተስማሙ እንደሆነ፦

፩/ ስምምነት የተደረሰው ኮሚሽኑ ከሚሰጠው ውሳኔ ሁኔታዎች ጋር በተገናኘ ሲሆን፣ ኮሚሽኑ በሁኔታዎቹ መሠረት ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

፪/ ስምምነት የተደረሰው በይግባኙ ክፊል ጉዳዮች ላይ ሲሆን፣ ኮሚሽኑ በይግባኙ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ የስምምነቱን ሁኔታዎች ተፈፃሚ ሊያደርግ ይችላል።

## ፲፪. ለባለስልጣኑ ስለሚመለስ ውሳኔ

፩/ ኮሚሽኑ በአዋጁ አንቀጽ ፺፩ መሠረት ይግባኝ የተጠየቀበትን ውሳኔ እንደገና እንዲመለከተው ለባለሥልጣኑ ሲመልስ፣ ባለሥልጣኑ ኮሚሽኑ

2/ If an applicant fails to appear in person or be represented at a hearing of the Commission, the Commission may dismiss the appeal.

3/ If an applicant fails to comply with the direction of the commission in relation to the appeal under consideration, the President may, on behalf of the Commission, dismiss the appeal.

4/ If the Commission has dismissed an appeal under sub-article (2) or (3) of this Article , the appellant may, within 30 days after receiving notification that the appeal has been dismissed, apply to the Commission for reinstatement of the appeal.

5/ If an application has been made under sub-article (4), the Commission may reinstate the appeal subject to any directions made by the President.

## 11. Agreement Between the Parties

If at any stage during an appeal, the parties agree in writing as to the terms of a decision of the Commission on the appeal or on a decision relating to part of the appeal:

1/ the Commission may make a decision in accordance with the terms of the agreement where the agreement relates to the terms of the decision of the Commission.

2/ the Commission may give effect to the terms of the agreement where the agreement reached relates to a decision on part of the appeal.

## 12. Decision to be Remitted to the Authority

1/ If, in accordance with Article 91 of the Proclamation, the Commission remits an appealable decision to the Authority for reconsideration, the Authority may,

የሰጠውን ትዕዛዝ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣

ሀ) ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ ማፅናት፤

ለ) ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ ማሻሻል፤ ወይም

ሐ) የአዋጁ አንቀጽ ፺፩(፮) ተፈፃሚ ሲሆን የታክስ ስሌቱን ከፍ ማድረግን ጨምሮ ይግባኝ የሚባልበትን ውሳኔ በመተው አዲስ ውሳኔ መስጠት፤

ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ይግባኝ የቀረበበትን ውሳኔ ሲያሻሽል ወይም አዲስ ውሣኔ ሲሠጥ የተሻሻለው ወይም የተሰጠው አዲስ ውሳኔ በኮሚሽኑ በይግባኝ እየታየ እንዳለ ይግባኝ የሚቀርብበት ውሳኔ የሚቆጠር ሲሆን፣ ይግባኝ ባዩ ባቀረበው ይግባኝ ሊቀጥል ወይም ይግባኙን ሊያነሳ ይችላል፡፡

**፲፫. ውሳኔ ስለማረም**

፩/ ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔ ወይም ውሳኔው የተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ ይዘት ስህተት እንዳለበት የተረዳ እንደሆነ፣ የውሳኔውን ወይም ውሳኔው የተመሠረተበትን የምክንያት መግለጫ ይዘት ሊያሻሽል ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሻሻለው ይዘት በኮሚሽኑ እንደተሰጠ ውሳኔ ይቆጠራል፡፡

፫/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የውሳኔ ወይም ውሳኔ የተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ ይዘት ስህተት፦

ሀ) የህትመት ወይም የአጻጻፍ ስህተትን፤ ወይም

ለ) በውሳኔ እና ውሳኔው በተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ መካከል የሚታይ ማንኛውንም አለመጣጣም፤

ይጨምራል፡፡

taking in to account the directions of the Commission:

a) affirm the appealable decision;

b) vary the appealable decision; or

c) set aside the appealable decision and make a new decision, including increasing a tax assessment when Article 91(6) of the Proclamation applies.

2/ When the Authority varies or sets aside an appealable decision in accordance with sub-article (1) of this Article , the decision as varied, or the new decision, shall be taken to be the appealable decision that is the subject of the appeal before the Commission and the appellant may either proceed with or withdraw the appeal.

**13. Correction of Decision**

1/ The Commission may alter the text of a decision or written statement of reasons for a decision if satisfied that there is an error in the text of the decision or the written statement of reasons.

2/ The altered text under sub-article (1) of this Article shall be treated as the decision of the Commission.

3/ For the purpose of this Article, an error in the text of a decision or statement of reasons includes:

a) a typographical or clerical error; or

b) any inconsistency between the decision and the statement of reasons.

## ምዕራፍ ሦስት

## የኮሚሽኑ አስተዳደር

### ፲፬. ስሚ የሚካሄድበት ቦታ

የኮሚሽኑ የክርክር ስሚዎች የኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት በሚወስነው ቦታ ይካሄዳሉ።ስለሆነም ስሚ የሚካሄድበትን ቦታ ኮሚሽኑ ለተከራካሪዎች ማሳወቅ አለበት።

### ፲፭. ወጪዎች

ተከራካሪዎች በክርክሩ ሂደት ያወጡትን ወጪ በሚመለከት ኮሚሽኑ ተገቢ እና ምክንያታዊ መስሎ የሚታየውን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

### ፲፮. ሰነዶችን ለኮሚሽኑ ስለማቅረብ

ለኮሚሽኑ ሊቀርብ የሚገባ ማንኛውም ሰነድ በኮሚሽኑ ሬጅስትራር በኩል መቅረብ አለበት።

### ፲፯. ሰነዶች የሚሰጡበት አድራሻ

ይግባኝ ባይ ከይግባኙ ጋር በተያያዘ ለሚሰጠው ማንኛውም ሰነድ አድራሻውን በጽሑፍ ማስታወቂያ ለሬጅስትራሩ መስጠት አለበት።

## ክፍል ስምንት

## ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

### ፲፰. የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ ስለመሆን

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ግለሰብ የሚከተሉትን መስፈርቶች ካሟላ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ እንደሆነ ሰው ይቆጠራል፦

ሀ) በታክስ፣ በሂሣብ አያያዝ፣በንግድ ሥራ፣በሕግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በማኔጅመንት ወይም በሌላ ተመሳሳይ የትምህርት ዓይነት ከዩኒቨርሲቲ ወይም ተመሳሳይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተሰጠ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት ማስረጃ ያለው እንደሆነ፤ እና

## CHAPTER THREE

## ADMINSTRATION OF THE COMMISSION

### 14. Place of Hearing

The hearings of the Commission shall take place at a location to be designated by the President of the Commission. Accordingly, the commission shall notify the parties the place of the hearing.

### 15. Costs

The Commission may make such order as it considers fair and reasonable regarding costs incurred by the parties in relation to the proceeding.

### 16. Filing of Documents with Commission

Any document required to be filed with the Commission shall be filed at the Registry of the Commission.

### 17. Address for Service of Documents

An appellant shall give the Registrar written notice of the appellant's address for service of any documents relating to the appeal.

## PART EIGHT

## LICENSING OF TAX AGENTS

### 18. Fit and Proper Person to Provide Tax Agent Services

1/ Subject to sub-articles (2) and (3) of this Article, an individual is a fit and proper person to provide tax agent services if the individual has:

a) aqualification of at least first degree in taxation, accounting, business, law, economics, management or other similar discipline; and

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት አምስት ዓመታት፦

(፩) ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል ክትትል ሥር በመሆን የታክስ ወኪልነት አገልግሎት በመስጠት፤ ወይም

(፪) እንደታክስ ሠራተኛ በማገልገል፤የሁለት ዓመት የሙሉ ጊዜ የሥራ ልምድ ያለው እንደሆነ።

፪/ አንድ ግለሰብ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ)(፩) ከተመለከተው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ ልምድ በሌላ ሀገር ያገኘ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ግለሰቡ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ)(፩) መስፈርት እንዳሟላ አድርጎ ሊወስደው ይችላል።

፫/ የሚከተሉት ግለሰቦች የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ እንደሆኑ ተደርገው አይቆጠሩም፦

ሀ) ዕዳውን መክፈል ያልቻለ ወይም መክሰሩ በፍርድ የተረጋገጠ ግለሰብ፤

ለ) በሥነ-ምግባር ጉድለት በሙያ ማህበር ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ግለሰብ፤

ሐ) ከእምነት ማጉደል ጋር በተገናኘ ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠና ቅጣቱን ፈፅሞ ያልተሰየመ ግለሰብ፤

መ) በተሻረው አዋጅ ጭምር የታክስ ግዴታውን ያለመወጣት ሪከርድ ያለበት ግለሰብ።

## ክፍል ዘጠኝ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፱.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

፩/ በተሻረው አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው "የቀድሞ ኮሚሽን" ተብሎ ለሚጠራው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የተሾሙ አባላት አገልግሎት በአዋጁ መሠረት "አዲሱ ኮሚሽን" ተብሎ የሚጠራው

b) at least 2 years of full-time experience in the previous 5 years in Ethiopia:

(1) in providing tax agent services under the supervision of a licensed tax agent; or

(2) as a tax officer.

2/ The Authority may regard an individual as satisfying sub-article (1)(b)(1) of this Article if the individual has experience equivalent to that specified in sub-article (1)(b)(1) of this Article in another jurisdiction.

3/ The following individuals are not regarded as a fit and proper person to provide tax agent services:

a) an individual who could not discharge his debt or who is a judicially declared bankrupt;

b) an individual who has been found guilty of misconduct by a professional body;

c) an individual who has been convicted of a criminal offence relating to dishonesty and who has not been reinstated;

d) an individual who has an unsatisfactory tax compliance record including under the repealed Proclamation.

## PART NINE
## MISCELLANEOUS

**19. Transitional Provisions**

1/ The appointment of a person as a member of the Tax Appeal Commission established under the repealed Proclamation (referred to as the "former Commission") shall terminate once the Tax Appeal Commission established under the Proclamation (referred to as the

የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ተቋቁሞ ሥራውን ሲጀምር ይቋረጣል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የሚመለከተው ሰው በአዋጁ አንቀጽ ፹፯ መሠረት ለአዲሱ ኮሚሽን አባልነት ለመታጨት ብቁ ይሆናል።

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፹፯(፫)(ለ) "የታክስ ሕግ" በሚል የተጠቀሰው የተሻረውን አዋጅ ይጨምራል።

፬/ ለቀድሞው ኮሚሽን የቀረበ ይግባኝ ኮሚሽኑ ሥራውን ከማቆሙ በፊት ውሳኔ ያላገኘ እንደሆነ፣ የአዲሱ ኮሚሽን ፕሬዚዳንት የሚሰጠው ማንኛውም ትዕዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ ይግባኙ በአዲሱ ኮሚሽን ውሳኔ ይሰጥበታል።

**፳. መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን**

ሚኒስትሩ ለዚህ ደንብ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**፳፩. ደንቡ የሚፀናበት ቀን**

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

"new Commission") comes into operation.

2/ A person to whom sub-article (1) of this Article applies shall be eligible for appointment as a member of the new Commission in accordance with Article 87 of the Proclamation.

3/ The reference in Article 87(3)(b) of the Proclamation to a "tax law" shall include the repealed Proclamation.

4/ If an appeal was filed with the former Commission and the appeal was not finalised before the former Commission ceased operations, the appeal shall be decided by the new Commission subject to any directions that the President of the new Commission may make.

**20. Power to Issue Directives**

The Minister may issue Directives for the proper implementation of this Regulation.

**21. Effective Date**

This Regulation shall enter in to force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 9th day of August 2017**

**Hailemariam Dessalegn**

**Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**